18ኛ ዓመት ቁጥር 12
18th Year No. 12

ባህር ዳር ሐምሌ 04 ቀን 2005 ዓ/ም
Bahir Dar, July 11/2013

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 15.00
Unit price Birr 15.00

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 203/2005 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ-ህዝብ ጉዳይ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

Content

Proclamation No. 203/2013

The Amhara National Regional State Population Affairs Council Establishment Proclamation

አዋጅ ቁጥር 203/2005 ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ-ህዝብ ጉዳይ ም/ቤትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ክልሉ ከስነ-ህዝብ ጉዳይ መልካም አጋጣሚዎች ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኝ በተደራጀ መልኩ መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በክልል ደረጃ በስነ-ህዝብ ጉዳዮች ዙሪያ ታማኒነት ያለውን መረጃ ለማዘጋጀት የሚያስችል ስርዓት መገንባት በማስፈለጉ፤

Proclamation No. 203/2013

A Proclamation to Provide for the Establishment of the Amhara National Regional State Population Affairs Council

WHEREAS, it is vital to make with an organized and coordinated effort, on population and development issues; so as to benefit the region from the demographic opportunities;

WHEREAS, there has been a great demand to establish a system; whereby, a reliable population data are generated at regional level.

በስነ-ህዝብ ዙሪያ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ለማካሄድ አስፈላጊውን የሰው ሃይል፣ቁሣቁስ እና ፋይናንስ ለማንቀሣቀስ በጉዳዩ ላይ ስልጣን ያለው አካል ማቋቋም ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

WHREAS, it has been of paramount importance to organize an authoritative body; to mobilize human, material and financial resources, in order to conduct a research and study, on population and development issues;

በወሊድ ብዛትና አራርቆ ባለመውለድ ሣቢያ ብሔራዊ ክልሉ በከፍተኛ የእናቶች ሞት የተጠቃ ከመሆኑ የተነሣ የክልሉ ልማት በሚፈለገው ፍጥነት ይራመድ ዘንድ በአሁኑ ወቅት ያለውን ያልተመጣጠነ የህዝብ ቁጥር እድገት ከልማቱ እድገት ጋር ማጣጣም አስፈላጊ በመሆኑ፤

WHEREAS, due to short spaced pregnancies and frequent child birth, the region is highly affected by maternal deaths. So that, it is necessary to harmonize the current unbalansed rate of population growth with that of the economic development; to pace the region's development with the relevant speed;

የስነ-ሕዝብ ጉዳይ በባህሪው ውስብስብና ዘርፈ-ብዙ ከመሆኑ አንፃር መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን፣ ድርጅቶችንና የህብረተሰብ ክፍሎችን ጥረት በማሰባሰብና ቅንጅታዊ አሠራር በመፍጠር ተጨባጭ ለውጥ ማምጣት በማስፈለጉ፤

WHEREAS, it has been found necessary; to bring tangible change through integrated approach in the region; hereby, to address the complex nature of population issues; it is vital to create a conducive environment, to coordinate the efforts of government bodies, non-government organizations and social groups of the society.

የችግሩን ጥልቀት አስቀድሞ የተረዳው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ሚያዚያ 1985 ዓ.ም የሀገሪቱን የስነ-ህዝብ ፖሊሲ ያወጣ በመሆኑና ይህንኑ ፖሊሲ ለማስፈፀም ክልላዊ መንግስታት የየራሣቸውን የስነ-ህዝብ ጉዳይ ም/ቤት ማቋቋም እንዳለባቸው በፖሊሲው ሰነድ አንቀጽ /6/ ላይ በግልጽ የተደነገገ በመሆኑ፤

WHEREAS, the Federal Democratic Republic of Ethiopia, that already understood the country's problem issued previously; the country's population policy in April 1993; and, proclaimed clearly, on Article 6 of the population policy; that the Regional Government; may establish their own public issues council, cause to implement this policy;

የአማራ ክልል ምክር ቤት በተሻሻለው የብሄራዊ ክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ /49/ንዑስ አንቀጽ 3/1/ ድንጋጌ ስር በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል፡፡

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional State, pursuant to, the power vested in it; under article 49 sub-article 3(1) of the National Region Revised Constitution, hereby issued this proclamation as follows.

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 203/2005 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ምክር ቤት" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ምክር ቤት ነው፤
2. "ቢሮ" ማለት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ነው፤
3. "ቦርድ" ማለት በምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ የሚሠየመው የስራ አመራር ቦርድ ነው፤
4. "ወሣኝ ኩነቶች" ማለት የልደት፣ የሞት፣ የጋብቻ፣ የፍች፣ የፍልሰትና ተመሣሣይ ማህበራዊ ክስተቶች አመልካች ሀረግ ነው።

ክፍል ሁለት

ስለ ም/ቤቱ መቋቋም፣ ዓላማና ስልጣን

3. ስለ ም/ቤቱ መቋቋም

1. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የስነ-ህዝብ ጉዳይ ም/ቤት ከዚህ በኋላ "ም/ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ህጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፤

PART ONE

GENERAL PROVISIONS

1) Short Title

This proclamation may be cited as "the Amhara National Regional State Population Affairs Council Establishment Proclamation No.203/2013"

2) Definition

Unless the context requires otherwise, in this proclamation:

1. 'Council' means the Amhara National Regional State Population Affairs Council.
2. 'Bureau' means the Amhara National Regional State Finance and Economic Development Bureau.
3. 'Board' means the Board that shall be nominated by the General Assembly of the Council.
4. 'Vital statistics means the indicator phrase of birth, death, marriage, migration, divorce and other similar social events.

PART TWO

ESTABLISHMENT OBJECTIVES, POWERS AND DUTIES OF THE COUNCIL

3. Establishment of the Council

1. The Amhara National Regional State Population Affairs Council, hereinafter called the Council, is established; pursuant to, this proclamation as a body, having its own autonomy and conferred with legal personality.

2. ም/ቤቱ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደርና በቀበሌ ደረጃ የሚዋቀሩ አካላት ይኖሩታል።

4. ዓላማዎች

ም/ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አበይት ዓላማዎች ይኖሩታል፦

1. የተቀናጀ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ አፈጻጸምን በማረጋገጥ ለክልሉ ዘላቂ ልማት አስተማማኝ መሠረት መጣል፤

2. እናቶች ያላቸውን በቤተሠብ እቅድ የመጠቀም መብት በማረጋገጥ በክልሉ ጤናማ እናትነትን ማስፈን።

5. ስለ ም/ቤቱ መደበኛ አድራሻ

1. የም/ቤቱ መደበኛ አድራሻ በባህር ዳር ከተማ ውስጥ ይሆናል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የሰፈረው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የየደረጃው ም/ቤቶች ቋሚ አድራሻ ም/ቤቶቹ በየተቋቋሙበት ስፍራ ይሆናል።

6. ስለ ም/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ስለ ብሔራዊው የስነ-ህዝብ ፖሊሲ አተገባበር በክልል ደረጃ አመራር ይሰጣል፤

2. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲውን አፈፃፀም በክልል ደረጃ ይገመግማል፣ አስፈላጊ ለውጦች እንዲካተቱ ለብሔራዊ የሥነ-ህዝብ ጉዳይ ምክር ቤት አስተያየት ይሰጣል፣ በነዚሁ ጉዳዮች ዙሪያ የክልሉን መንግስት ያማክራል፤

3. ክልል አቀፍ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ የድርጊት መርሀ-ግብር እንዲዘጋጅና ተግባራዊ እንዲሆን፣ እንዲሁም በልማት ማዕቀፍ ውስጥ በተሟላ መልኩ እንዲካተት አመራር ይሰጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

2. The council, shall have organs that shall be organized in Regional, zonal woreda or city Administration and at the kebele levels.

4. Objectives

The council shall have the following two major objectives; pursuant to this proclamation:

1. To lay a reliable foundation for the region's sustainable development, by enhancing an organized and integrated population affairs activities,

2. Strive to bring safe motherhood in the region, through maintaining the right of mothers; to access and use family planning services.

5. Regular Address of the Council

1. The regular address of the council shall be in Bahir Dar City Administration.

2. Without prejudice to the general provisions,stipulated under sub-article(1) of this Article, the regular address of each council at different levels, shall be at the place where council is established.

6. Powers and Duties of The Council

The council shall have the following powers and duties, pursuant to this proclamation,

1.Give guidance on the implementation of the national population policy at the regional level;

2. Evaluate the implementation of the population policy throughout the region; and, give comments to the national population council, in order to incorporate the necessary changes; thereby rendering advice, to the regional government on these issues;

3.Give guidance for the preparation and implementation of population plan of action; as well as, render leadership role, monitor and evaluate its implementation, to be incorporated in the development framework of the region appropriately,

4. በተለያዩ የክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚካሄዱት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሥነ-ህዝብ ፖሊሲውና በክልሉ ስነ-ህዝብ ጉዳይ ምክር ቤት መመሪያ መሠረት መከናወናቸውን ይከታተላል፤

4.Monitor and render a leadership role ,whether the implementation of programs and projects run by different sectors of the regional government is in consistent with the population policy; and, its guideline of the council of the population;

5. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲውን ከመተግበር አኳያ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የክልሉ መንግስት መሥሪያ ቤቶች መካከል ቅንጅታዊ አሠራር መፈጠሩንና የሲቪል ማህበረሰቡም ሆነ የግሉ ዘርፍ በአግባቡ መሳተፋቸውን ያረጋግጣል፤

5. Confirm that whether in the process of implementing the population policy; the activities are intertwined and performed between the pertinent regional government sectors, in an integrated and coordinated manner ; and, whether civic societies and the private sectors are actively participate in this effort;

6. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲውን አፈጻጸም አስመልክቶ ለክልሉ ምክር ቤት ወቅታዊ ሪፖርቶችን ያቀርባል፤

6.Submit periodic report of the implementation of population policy to the Council of Amhara Region;

7. የተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን በማሳተፍ ከሥነ-ሕዝብና ልማት ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ለህብረተሰቡ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

7.Create a favorable working climate to dissminte data to the public; that are directly related to the population and development; through full participation of the government and non-governmental organizations;

8. ለስነ-ሕዝብ ጉዳይ ማስፈፀሚያ የሚሆን ሀብት በተጠናከረ አኳኋን እንዲሰበሰብና በአግባቡ በሥራ ላይ እንዲውል አመራር ይሠጣል፣አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

8.Provide guidance and follow-up the resource to be collected in a strengthened way; and, properly put in effect, cause to implement for the population policy thereof;

9.ሰብሳቢውን ጨምሮ የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይሰይማል፣ ከሀላፊነት ያነሣል፤

9. Nominate; dismiss members of the executive board including its chair person;

10. በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደርና በቀበሌ ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ተግባራቸውን ይደግፋል፤

10. Create a favorable climate ;whereby, population affairs councils to be established at zonal, woreda, city/town administration and kebele levels;

11. የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው በክልል ደረጃ ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲተገበር አስፈላጊ ሆኖ የተገኙትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

11. Perform other related activities that are necessary for being effective and result oriented implementation of the population policy, at regional level.

ክፍል ሦስት

ስለ ም/ቤቱ አደረጃጀትና ተዋረዳዊ አወቃቀር

7. ስለ ም/ቤቱ የስልጣን አካላት

ም/ቤቱ በክልል ደረጃ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ እና
2. የሥራ አመራር ቦርድ፡፡

8. ስለ ጠቅላላ ጉባኤው አመሰራረትና የአባላት ጥንቅር

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ አዋጅ መሠረት የምክር ቤቱ ከፍተኛ የስልጣን አካል ሆኖ የተመሰረተ ሲሆን ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የክልሉ ርዕሠ መስተዳድር.....ሰብሳቢ

ለ/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሀላፊ .....አባልና ፀሐፊ

ሐ/ የጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ .....አባል

መ/ የትምህርት ቢሮ ኃላፊ.....አባል

ሠ/ የቴክኒክ፣ ሙያና ኢንተርፕራይዞች ልማት ቢሮ ኃላፊ ..... አባል

ረ/የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ.....አባል

ሰ/ የሴቶች፣ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ..... አባል

ሸ/ የግብርና ቢሮ ኃላፊ.....አባል

ቀ/የሲቪል ሰርቪስ ቢሮ ኃላፊ.....አባል

በ/የፍትህ ቢሮ ኃላፊ.....አባል

ተ/ የባህል፣ቱሪዝምና ፓርኮች ልማት ቢሮ ኃላፊ .....አባል

ቸ/ የኢንዱስትሪና ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ..... አባል

PART THREE

HIGHRARCHIAL STRUCTURE AND ORGANIZATION OF THE COUNCIL

7. Organs of Power of the Council

The council shall have, the following organs of power at the regional level:

1. General Assembly; and,
2. Board of Management

8. Foormation of the General Assembly and Its Composition

1. The General Assembly pursuant to this proclamation,is the supreme organ of power vested in the council; and, it shall have the following members:

a) The Regional Head of Government....chairperson

b) Head of the Bureau of Finance and Economic Development ..... (Member and secretary)

c) Head of the Bureau of Health.....member

d) Head of the Bureau of Education, ...member

e) Head of the Bureau of Technic, Vocational and Interprises Development ..... member

f) Head of the Bureau of Labor and Social Affairs ..... member

g) Head of the Bureau of Women,Children and Youth Affairs..... member

h) Head of the Bureau of Agriculture..... member

i) Head of the Bureau of Civil Service..... member

j) Head of the Bureau of Justice ..... member

k) Head of the Bureau of Culture, Tourism and Parks Development ..... member

l) Head of Bureau of Industry and Urban Development ..... member

ኃ/ የአካባቢ ጥበቃ፣ የገጠር መሬት አስ/ና አጠ/ቢሮ ኃላፊ.....አባል

ነ/ የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ኃላፊ .....አባል

ኘ/ የአደጋ መከላከልና ምግብ ዋስት‹ናፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ኃላፊ..... አባል

አ/ የስፖርት ኮሚሽን ኮሚሽነር..... አባል

ከ/የህብረት ሥራ ማህበራት ማስ/ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ..... አባል

ኸ/ የግብርና ምርምር ተቋም ዋና ዳይሬክተር..... አባል

ወ/ በማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን የክልሉ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ ..... አባል

ዐ/ የባ/ዳር ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት ወይም ተወካይ..... አባል

ዘ/ በክልሉ ውስጥ የሚገኙትን የሀይማኖት ተቋማት በበላይነት የሚመሩ ኃላፊዎች..... አባላት

ዠ/ የክልሉ ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር አባል

የ/ የክልሉ ሴቶች ማህበር ሊቀመንበር..... አባል

ደ/ የክልሉ መምህራን ማህበር ሊቀመንበር..... አባል

ጀ/ በስነ-ህዝብ ጉዳዮች ላይ አተኩረው የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ሀላፊዎች ..... አባላት

ገ/ በዞንና በሜትሮፖሊታንት ከተማ አስተዳደሮች የሚገኙ የስነ-ህዝብ ጉዳይ ም/ቤቶች ሰብሳቢዎች.....አባላት፡፡

m) Head of the Bureau of Environmental Protection, Land Administration and Use ..... member

n) Head of the communication Affairs Office..... member

o) Head of the Disaster Prevention and Food Security Program Coordination Office ..... member

p) Commissioner of the sport Commission..... member

q) Head of the Cooperatives Development Agency ..... member

r) Head of the Regional Agricultural Research Institute..... member

s) Head of the Central Statistics Agency Branch Office of the Region..... member

t) President or delegatee of the Bahir Dar University..... member

u) Heads, who preside over religious institutions superiorly in the region..... members

v) Chairperson of Regional Youth Association..... member

w) Chairperson of Regional Women's Association..... member

x) Chairperson of Regional Teachers' Association..... member

y) Heads of Non-Govermental organizations working on population affairs at the regional level..... member

z) Chair persons of the population Affairs Councils of the zone and the metropolitant city administrations. ..... member

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተመለከተው ቢኖርም፣ ሌሎች አካላት የዚሁ ም/ቤት አባል ለመሆን ጥያቄ ሲያቀርቡ፣ የአባልነት ጥያቄያቸው በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በኩል ቀርቦ በሥራ አመራር ቦርዱ የሚወሰን ይሆናል፤

2. Notwithstanding, the stipulated issue of sub-article /1/ of this Article, where other Organizations request for membership of the Council, their requests shall be decided upon by the board of management, being forwarded to the Regional Finance and Economic Development Bureau.

3. የጉባኤው አባላት መብቶችና ግዴታዎች ዝርዝር ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም ወደፊት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

3. The particular Rights and Duties of members of the Assembly, shall be determined by a Regulation that shall be issued; for the implementation of this proclamation.

9. <u>የጠቅላላ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የአገሪቱ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ ተግባራዊ መሆኑን ይከታተላል፤
2. ክልል አቀፍ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ድርጊት መርሐ-ግብር እንዲዘጋጅና ተፈፃሚ እንዲሆን ያደርጋል፤
3. የስራ አመራር ቦርዱን አባላት ይመርጣል፣ከሀላፊነት ያነሳል፤
4. በስራ አመራር ቦርዱ አማካኝነት የሚቀርቡለትን አመታዊ የስራ እቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቆች መርምሮ ያፀድቃል፤
5. ለስራ አመራር ቦርዱ አጠቃላይ የስራ መመሪያ ይሠጣል፣ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤
6. የስነ-ሕዝብ ፖሊሲውን ሊያሣኩ የሚችሉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

9. <u>Powers and Duties of The General Assembly</u>

The General Assembly, shall have the following particular powers and duties, pursuant to this proclamation:

1. Follow up, the implementation of the Ethiopian population policy in the region,
2. Give guidance for the preparation and execution of Regional Population plan of action
3. Elect members of the Board of management; dismiss them from their responsibilities,
4. Approve the annual work plan and executioner budget; where the draft is submitted by the Board of management.
5. Give comprehensive guidance to the board of management; with respect to its duties; follow-up and supervise the execution thereof;
6. Carry out other duties that help to accomplish population policy.

10. ስለ ጠቅላላ ጉባኤው አመራር፣ ስብሰባና የአሠራር ስነ-ስርዓት

1. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር የም/ቤቱ የበላይ ጠባቂ በመሆን ጠቅላላ ጉባኤውን ይመራል፤
2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ የጠቅላላ ጉባኤው ፀኃፊ በመሆን ያገለግላል፤
3. ጠቅላላ ጉባኤው በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባዎችን ያካሂዳል፣እንደአስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ሊያደርግ ይችላል፤
4. ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ውስጥ 2/3ኛው የተገኙ እንደሆነ ምልዐተ-ጉባኤ ይሆናል፤
5. ማናቸውም የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምጽ ያልፋል፡፡ ሆኖም ድምጹ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን የጉባኤው ውሣኔ ይሆናል፤
6. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ/1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /5/ የሠፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ጉባኤው የራሱን የስብሰባና የአሠራር ስነ-ስርዓት የሚመለከቱ ዝርዝር መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

10. Leadership, Meeting and Procedure of the General Assembly

1. The Regional Head of Government shall preside over the General Assembly, being a superior auspices of the Council,
2. The Head of Bureau of Finance and Economic Development shall serve as the secretariat of the General Assembly,
4. The General Assembly shall hold its regular meetings twice a year; as deemed as necessary, it may also conduct urgent meetings,
4. There shall be a quorum where two-thirds of the members show up at any meeting of the general assembly,
5. Decision of the general assembly shall be passed by a majority vote of its members present at a meeting provided, however, that the chair person may have a casting vote in case of a tie,
6. Without prejudice to the provision of sub-Arts./1/ through /5/ of this article hereof, the assembly may issue specific guidelines with regard to its own meetings and working procedures,

11. የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሣቢ ስልጣንና ተግባር

የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሣቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የጠቅላላ ጉባኤውን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይመራል፤
2. የሥራ አመራር ቦርዱን እንቅስቃሴ በቅርብ ይከታተላል፤

11. Powers and Duties of The Chairperson of the General Assembly

The chairperson of the general assembly shall have the following powers and duties:

1. Preside over the regular and urgent meetings of the General Assembly,
2. Closely monitor the activities of the board of management,

3. መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለም/ቤቱ አስፈላጊውን እገዛ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

4. በስነ-ሕዝብ ዙሪያ በሚደረጉ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ ይሳተፋል፣ ወይም ሌሎች እንዲገኙ ይወክላል፤

5. የም/ቤቱ ገንዘብና ንብረት በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

6. አስፈላጊ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ የም/ቤቱ የሂሣብ መዛግብት በታወቁ የሂሣብ ባለሙያዎች እንዲመረመሩ ያደርጋል፤

7. በጉባኤው የሚሰጡትንና ከዚህ አዋጅ ጋር የማይቃረኑትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

3. Create a conducive environment for Governmental and Non-Governmental organizations, to render the necessary assistance to the council,

4. Participate at national and international conferences dealing with population issues, or authorize others for the purpose,

5. Follow- up and oversee the proper implementation of the financial and proprietary provisions of the council,

6. Cause the books of account in the possessions of the council be audited by recognized accountants, whenever he is convinced that such action is necessary.

7. Perform other related activities; that are rendered by the assembly and not inconsistent with this proclamation.

12. ስለ ስራ አመራር ቦርዱ አሰያየምና የአሠራር ሥነ- ሥርዓት

12. Designation and Working Procedures of The Board of Mmanagement

1. ም/ቤቱ በጠቅላላ ጉባኤው ምርጫ የሚሰየምና ከአምስት እስከ ሰባት አባላት ያሉት የራሱ የሥራ አመራር ቦርድ ይኖረዋል፤

1. The council shall have board of management of its own to be designated by the General Assembly; and, shall have members from five to seven in number,

2. የቦርዱ ተጠሪነት ለጠቅላላ ጉባኤውና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳደር ይሆናል፤

2. The Accountability of the Board shall be to the General Assembly and the Head of the Regional Government,

3. ቦርዱ ቢያንስ በ3 ወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣ እንደአስፈላጊነቱም አስቸኳይ ስብሰባዎችን ያደርጋል፤

3. The General Assembly shall hold its regular meetings at least once in 3 menths , as deemed as, necessary, it may also conduct urgent meetings,

4. ከቦርዱ አባላቱ ውስጥ 2/3ኛው በስብሰባው ላይ የተገኙ እንደሆነ ምልዓተ-ጉባኤ ይሆናል፤

4. There shall be a quorum, where two-third of the members, presented at the meeting;

5. ማናቸውም ጉዳይ በስብሰባው ላይ በተገኙት አባላት የአብላጫ ድምጽ ከተደገፈ የቦርዱ ውሣኔ ሆኖ ያልፋል። ሆኖም ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሣቢው የደገፈው ወገን የቦርዱ ውሣኔ ይሆናል፤

5. Decision of the General Assembly shall be passed by a majority vote of its members present at a meeting .Notwithstanding, the Chairperson may have a casting vote in case of a tie,

6. ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ /1/ እስከ ንዑስ አንቀጽ /5/ የሰፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ቦርዱ የራሱን የስብሰባና የአሠራር ስነ-ሥርዓት መመሪያዎችን አውጥቶ በሥራ ላይ ሊያውል ይችላል፡፡

13. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. የም/ቤቱ ሥራ አስፈፃሚ አካል በመሆን ይሠራል፤
2. ከለጋሽ ግለሰቦች፣ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከሃይማኖት ተቋማትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የጠበቀ የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤
3. በስነ-ሕዝብ ጉዳይ ላይ የሚሠሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴዎች ያስተባብራል፣ በመካከላቸውም የሥራ ቅንጅት እንዲኖር ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤
4. በክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በኩል ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ ገምግሞ ከአስተያየት ጋር ለጠቅላላ ጉባኤው በማቅረብ ያስፀድቃል፤
5. በበጀት ውስጥ አስቀድሞ ያልተመለከተ ገቢ በሚገኝበት ጊዜ በሥራ ላይ እንዲውል ካረደገ በኋላ ጠቅላላ ጉባኤው ሲሰበሰብ ይህንኑ አቅርቦ ያስፀድቃል፤
6. ጠቅላላ ጉባኤው በማይሰበሰብበት ጊዜ ለም/ቤቱ አባልነት የሚቀርቡ ጥያቄዎችን መርምሮ ያፀድቃል፤

6. Without prejudice to the provision of sub-arts /1/ through /5 /of this Article hereof, the Board may issue specific guidelines with regard to its own meetings and working procedures

13.<u>Powers and Duties of The Board</u>

Pursuant to this proclamation, the board of management, shall have the following powers and duties:

1. Serve as an executive organ of the council,
2. Create close and strengthened working relationship with private donors, governmental and non-governmental organizations, religious and international organizations,
3. Coordinate the activities of governmental and non-governmental organizations working on population issues ; and, create suitable conditions for integration of efforts,
4. Evaluate the draft annual work plan and executioner budget proposal, prepared and submitted to it, by the Finance and Economic Development Bureau; and, have same approval by the general assembly, upon the presentation with its own preliminary opinion,
5. Where an unindicated income, that was not previously stated, is found in the Budget after implementing it cause approval this budget, where General Assembly conducts a meeting,
6. Evaluate and thereby approve requests forwarded for membership of the council; when the General Assembly is not conducting meetings;

7. በጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉትን ውሣኔዎችና የሚሰጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ያደርጋል፤
8. ስለአከናወናቸው ተግባራት በየጊዜው ለጠቅላላ ጉባኤው ሪፖርት ያቀርባል፤
9. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የክልሉ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ እንቅስቃሴ ከአገር አቀፍ እና ከዓለም አቀፍ ተመሣሣይ አካላት ጋር ጠንካራ ግንኙነት እንዲኖረው ያደርጋል፤
10. የስነ-ሕዝብ ጉዳዮችን በተመለከተ በሚካሄዱ አገር አቀፍ እና ዓለም አቀፍ ስብሰባዎች በሰብሳቢው ወይም በሌሎች ተወካዩቹ አማካኝነት ይካፈላል፤
11. አስፈላጊ በሆነበት ጊዜ ለስራው አጋዥ የሆኑ አደረጃጀቶችን ያቋቁማል፤
12. በስነ-ሕዝብ ጉዳይ ላይ በተለያዩ አካላት ተቀርፀው የሚቀርቡለትን ፕሮግራሞች እና ፕሮጀክቶች ይገመግማል፣ያፀድቃል።

7. Put in effect decisions passed and instructions handed down to it by the General Assembly,
8. Submit periodic reports to the General Assembly in accordance with the activities undertaken;
9. See to it the strengthened ties and cooperations are maintained with national and global organizations at the national and international levels in view of addressing population and related issues in collabretion with those concerned;
10. Take part in any national and global meetings aimed at addressing population affairs via chair Person or other delegatees from board members;
11. Put in place helpful organizational setups for activities; where, as deemed as, necessary;
12. Evaluate and thereby approve programs and projects on population issues addressed to it and drafted from different bodies,

14. ስለ ቢሮው ተግባርና ሀላፊነት

በዚህ አዋጅ አንቀጽ /9/ እና አንቀጽ /13/ ሥር እንደአግባብነቱ ለጠቅላላ ጉባኤው እና ለሥራ አመራር ቦርዱ የተሰጧቸው ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው፣ ቢሮው የስነ-ህዝብ ጉዳዮችን በተመለከተ የሚከተሉት ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

14. Powers and Duties of The Bureau

Without prejudice to, the general duties and responsibilities bestowed, upon the General Assembly and the Board of Management, under articles/ 9/ and /13/ of this proclamation hereof; the Bureau shall have the following particular duties and responsibilities inaccordance with population affairs:

1. ለጠቅላላ ጉባኤውና ለስራ አመራር ቦርዱ ሴክሬታሪያት ሆኖ ያገለግላል፣ እንዲሁም በዞን፣ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደርና በቀበሌ ደረጃ ለሚቋቋሙ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ምክር ቤቶች ተፈላጊውን የሙያ ድጋፍ ይሰጣል፤

2. የክልሉን የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ረገድ ለቦርዱ ቴክኒካዊ ድጋፍ ይሰጣል፣ የመርሃ-ግብሩን አፈፃፀምም ይከታተላል፤

3. በክልሉ ውስጥ በተለያዩ መንግሥታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚካሄዱ የሥነ-ሕዝብ ተግባራት እንዲቀናጁ ያስተባብራል፤

4. በክልል ደረጃ የሥነ-ሕዝብ ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና ኮሙኒኬሽን ስትራቴጂ እንዲቀረጽ ያደርጋል፣ ስራውን በበላይነት ያስተባብራል፤

5. በተለያዩ የክልሉ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች እና ሌሎች ድርጅቶች የሚካሄዱ የልማት ፕሮግራሞች ከሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው ጋር በተጣጣመ መንገድ መተግበራቸውን በቅርብ ይከታተላል፣ይደግፋል፤

6. ዓመታዊ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ መጽሔት እንዲታተም ያደርጋል፤

7. ክልል አቀፍ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ የመረጃ ቋት እንዲመሠረት ያደርጋል፤

8. ከወሣኝ ኩነቶች የምዝገባ ሥርዓት በሚገኘው መረጃ ላይ ተመስርቶ ክልላዊውን የስነ-ህዝብ መረጃ በየጊዜው ይከልሣል፣ ውጤቱንም ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል፤

1. The bureau shall serve as the secretariat of the General Assembly and the board of management; and give technical support to the population Affairs councils at the zone, woreda or city administration and the kebele levels,

2. Provide technical support, in the process of preparation of the action plan of the Regional population affairs and follow-up its execution,

3. Coordinate activities being conducted on population issues, that shall be integrated by governmental and non-governmental organizations,

4. Cause to be designed the Population Information, Education and Communication Strategy, at the Regional level and coordinate duties superiorly;

5. Follow up closely and support whether the implementation of development programs and projects run by different regional sectors and by other organizations, is consistent with the population policy ,

6.Publish annul magazine on population issues,

7. Establish Regional Population Affairs Data Base,

8. Revise the regional population data frequently; based on the data generated from the vital registrations system; disseminate the result to beneficiaries,

9. የክልሉ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ መረጃ በቀበሌ ደረጃ በየዓመቱ እየተተነበየ ለተጠቃሚዎች በወቅቱ እንዲሰራጭ ያደርጋል፤

9. Distributes regional data to users timely, regarding to population issues at the kebele level predicting annually,

10. በሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ጥናትና ምርምር እንዲካሄድ ጥረት ያደርጋል፤

10. Make the necessary effort to conduct studies and researches on population issues,

11. የሥነ-ሕዝብ ጉዳዮች በልማት ዕቅድ ዝግጅትና ክትትል ሂደት በተሟላ ሁኔታ እንዲካተቱ ለፈፃሚ ተቋማት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፤

11. Provide the necessary support, to executioner institutions on population issues; to be included appropriately in the preparation of development plans and in the process of monitoring,

12. በክልል ደረጃ ከተለያዩ ለጋሽ ድርጅቶች የገንዘብ፣ የሙያና የማቴሪያል ድጋፍ ለማስገኘት ጥረት ያደርጋል፤

12. Devise a strategy aimed at gaining financial, technical and material support from different donor organizations at the regional level,

13. በሥነ-ሕዝብና ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ክልል አቀፍ ጉባኤዎች፣ ሲምፖዚየሞች፣ ሴሚናሮችና መሰል አውደ-ጥናቶች እንዲዘጋጁ ያደርጋል፤

13. Prepare Regional Level confences, Symposiums, Seminars and the like on population issues,

14. በሥነ-ሕዝብና ተያያዥነት ባላቸው መስኮች ሥልጠናና ምርምር ለማካሄድ የሚያስችል አቅም በክልል ደረጃ እንዲጠናከር ጥረት ያደርጋል፤

14. Put an effort to strengthen training and research capacity of the region on population and related issues,

15. ረቂቅ ዓመታዊ የስነ-ህዝብ ጉዳይ የድርጊት መርሀ-ግብርና በጀት ያዘጋጃል፤

15. Prepare draft annual action plan of population affairs and executioner budget,

16. ክልላዊ የስነ-ሕዝብ ጉዳዮችን አስመልክቶ የተጠቃለለ ሪፖርት ያዘጋጃል፤

16. Prepare a comprehensive regional annual reports on population issues,

17. በጠቅላላ ጉባዔውና በስራ አመራር ቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል።

17. Carry out other related additional activities, that are rendered by the General Assembly and the Board of Manegement.

ክፍል አራት

ስለ ም/ቤቱ የተዋረድ እርከኖች አደረጃጀትና ሥልጣን

PART FOUR

ORGANIATION and POWERS OF THE HIERARCHICAL TIERS OF THE COUNCIL

15. ዞን አቀፍ አደረጃጀት

በዚህ አዋጅ መሠረት በዞን ደረጃ የሚዋቀረው ም/ቤት የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፦

1. የዞን ጠቅላላ ጉባኤ፤ እና

15. Zonal Organizations

Pursunt to this proclamation,the council that shall be organized at zonal level, shall have the following organs:

1.The General Assembly of zone; and,

2. የሥራ አመራር ኮሚቴ።

16. ስለ ዞን ጠቅላላ ጉባኤ አመሰራረትና የአባላት ጥንቅር

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ /8/ ንዑስ አንቀጽ /1/ ስር የተዘረዘሩት መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶች፣ ድርጅቶች ፣የሀይማኖት ተቋማት፣ እንዲሁም ህዝባዊያንና የሙያ ማህበራት በዞኑ ውስጥ ቅርንጫፎች፣ ተጠሪና ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ያሏቸው እንደሆነ የነዚሁ አካላት የበላይ ሀላፊዎች እንደየአግባብነታቸው የዞን የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት አባላት ይሆናሉ።
2. የዞን ጠቅላላ ጉባኤ በዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ይመራል።

17. ስለዞን ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰያየም፣ ተጠሪነትና ተግባር

1. የዞን የሥራ አመራር ኮሚቴ በዞኑ ጠቅላላ ጉባኤ ተመርጦ የሚሰየምና አምስት አባላት ያሉት የዞን ም/ቤት አስፈጻሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤውና ለዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል፤
2. የዞን የሥራ አመራር ኮሚቴ በዞን ደረጃ የሚከናወኑ የስነ-ሕዝብ ተግባራትን በተጠናከረ መንገድ ለማስተባበርና ለመከታተል የሚያስችል አጠቃላይ ስልጣን፣ ተግባርና ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

18. ወረዳ አቀፍ አደረጃጀት

ም/ቤቱ በወረዳ ደረጃ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ፤ እና
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ።

2.The management committee,

16. Formation of General Assembly of Zone and its Composition of Members

1. The particulars, that are stated under sub-article /1/ of Article /8/ of this proclamation, the government as well as the non-governmental sectors, organizations, religious institutions as well as public and professional associations in the zone; senior officials of these bodies, as deemed as, necessary, shall be the zone population affairs council members.
2. The General Assembly of zone shall be presided over by the chief administrator of zone.

17. Designation, Accountability and Duties of Management Committee of the Zone

1. The management committee of the zone having been elected by the zonal General Assembly, shall have five members; and, serve as an executive body of the zone council and being accountable to the zone General Assembly and the chief administrator of the zone concerned thereof.
2. The zone management committee shall have comprehensive powers, duties and responsibilities to create an enabling environment to strongly coordinate and follow up the activities with respect to population issues,

18. Organization of the Woreda Level Council

The Council shall have the following Organs in the Woreda Level:

1.The General Assembly,and,

2.The Management Committee.

19. ስለ ወረዳ ጠቅላላ ጉባኤ አመሠራረትና የአባላት ጥንቅር

1. የዚህን አዋጅ አንቀፅ /8/ ንዑስ አንቀፅ /1/ ድንጋጌ መነሻ በማድረግ ከዚህ በላይ በአንቀፅ /16/ ንዑስ አንቀፅ /1/ ስር የተመለከቱት መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ያልሆኑ መ/ቤቶች፣ ድርጅቶች፣ የሀይማኖት ተቋማት፣ እንዲሁም ህዝባዊያንና የሙያ ማህበራት በወረዳው ውስጥ ቅርንጫፎች፣ ተጠሪና ማስተባበሪያ ጽ/ቤቶች ያሏቸው እንደሆነ የእነዚሁ አካላት የበላይ ሀላፊዎች እንደየአግባብነታቸው የወረዳ ስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት አባላት ይሆናሉ፤
2. በወረዳ ደረጃ የሚቋቋመው የም/ቤቱ ጠቅላላ ጉባኤ በወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ይመራል።

20. ስለ ወረዳ ሥራ አመራር ኮሚቴ አሰያየም፣ ተጠሪነትና ስልጣን

1. የወረዳ የሥራ አመራር ኮሚቴ በወረዳ ጠቅላላ-ጉባኤ ተመርጦ የሚሰየምና አምስት አባላት ያሉት የወረዳው ስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት አስፈጻሚ አካል ሲሆን፣ ተጠሪነቱ ለጠቅላላ ጉባኤውና ለወረዳው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል፤
2. የወረዳ የሥራ አመራር ኮሚቴ በወረዳ ደረጃ የሚከናወኑ የስነ-ሕዝብ ተግባራትን በተጠናከረ መንገድ ለማስተባበርና ለመከታተል የሚያስችል ስልጣንና ሀላፊነት ተሰጥቶታል።

19. Formation of General Assembly of Woreda and its Composition of Members

1. In accordance with sub article /1/ of Article /8/ of this proclamation , the stipulated ones; in sub –article /1/ of here in above Article /16/, the government, as well as the non-governmental sectors, organizations, religious institutions as well as public and professional associations in the worda; senior officials of these bodies, as deemed as, necessary, shall be the woreda population affairs council members.
2. The General Assembly of the population affairs council, that shall be organized at the woreda level, shall be presided by the chief administrator of the woreda.

20. Designation, Accountability and Power of the Woreda Management Committee

1. The Management Committee of the Woreda , having been elected by the Woreda General Assembly of population affairs council , shall have five members and serve as an executive body of the Woreda population affairs Council; and is accountable to the Woreda Assembly and the Chief Administrator of the Woreda thereof.
2. The Woreda Management Committee shall have duties and responsibilities to create an enabling environment, to strongly coordinate and follow up the activities with respect to population issues.

21. በከተማ አስተዳደር ደረጃ ስለሚቋቋም የስነ ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት

የም/ቤቱን ወረዳ አቀፍ አደረጃጀት አስመልክቶ በዚህ አዋጅ ከአንቀፅ /18/ እስከ /20/ የተዓፉት ድንጋጌዎች በከተማ አስተዳደር ደረጃ ለሚቋቋመው የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ምክር ቤትም በተመሣሣይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

22. በተዛማጅ ድንጋጌዎች ስለመስራት

1. በዞንና በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ደረጃ ይህንን አዋጅ መሠረት አድርገው የተቋቋሙ የዞን፣ የወረዳ ወይም የከተማ አስተዳደር ጠቅላላ ጉባኤዎችና የሥራ አመራር ኮሚቴዎች በየተደራጁባቸው አካባቢዎች ውስጥ እንደ አግባብነቱ የክልል ስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት ጠቅላላ ጉባኤና የሥራ አመራር ቦርድ አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /9/ እና /13/ ስር የሰፈሩትን ድንጋጌዎች ሊሠሩባቸው ይችላሉ፡፡

23. ቀበሌ አቀፍ አደረጃጀት

ምክር ቤቱ በቀበሌ ደረጃ የሚከተሉት አካላት ይኖሩታል፡-

1. ጠቅላላ ጉባኤ እና
2. የሥራ አመራር ኮሚቴ፡፡

24. ስለ ቀበሌ ጠቅላላ ጉባኤ አወቃቀር፣ የአባላት ተዋጽዎ፣ ኃላፊነትና አሠራር

1. በቀበሌ ደረጃ የሚመሰረተው የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ.....ሰብሳቢ

ለ/ የቀበሌው ሥራ አስኪያጅ.....አባልና ፀሐፊ

21. Council of Population Affairs Established with City Administration

In accordance with the council's organization of the woreda, the provisions issued from Article /18/ up to Article /20/ of this proclamation, shall have applicability, to be established with the standard of the city's population affairs council.

22. Working on the related provisions

1. The zone, the woreda or the city administration General Assemblies and the management committees, being established at the Zonal or the woreda or the city administrations level; pursuant to this proclamation, within the boundaries of their respective zone, woreda or city Administration, be able to use of those stipulated provisions, under Articles /9/ and /13/ of this proclamation, intaccordance with the General Assembly of population affairs council and the board of management of the regional level.

23. Organization of the Kebele Population Council

The Council shall have the following organs, to be organized at the kebele level.

1. The General Assembly, and
2. The management Committee

24. Structure, Composition of Members, Responsibility and working Procedures of the General Assembly of the Kebele

1. The General Assembly of the population affairs council, that shall be established at the kebele level shall have the following members, pursuant to this proclamation.
   a. Chief administrator of the kebele…….. chairperson
   b. Manager of the kebele ... Member and secretary

ሐ/ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ መንግስታዊያን ተቋማት ኃላፊዎች.....አባላት

መ/ በቀበሌው ውስጥ የሚሠሩ የጤና ኤክስቴንሽን ሠራተኞች.....አባላት

ሠ/በቀበሌው ውስጥ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ኃላፊዎች.....አባላት

ረ/ በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ የሃይማኖት መሪዎች.....አባላት

ሰ/ በቀበሌው ውስጥ የሚኖሩ ታዋቂ ግለሰቦች ወይም የማህበረሰብ ተጠሪዎች.....አባላት

ሸ/ የቀበሌው ወጣቶች ማህበር ሊቀመንበር .....አባል

ቀ/ የቀበሌው ሴቶች ማህበር ሊቀመንበር.....አባል

በ/ በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጡ ሌሎች አካላትና ግለሰቦች.....አባላት

c. Heads of government institutions of the kebele ….. members

d. Helath extension agenets of the kebele …….. members

e. Heads of the Non-Governmental organizations who work in the kebele…… members

f. Religious leaders of the kebele …… members

g. Prominent individuals of the kebele or community leaders …… members

h. Chairperson of Youth Association of the kebele …… member

i. Chairperson of the kebele women's association…….. member

j. Other privates and Individuals that shall be clected, by the General Assembly of the kebele…….. members

2. ጠቅላላ ጉባኤው በቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ የሚመራ ይሆናል;

2. The General Assembly shall be presided over by the chief administrator of the kebele;

3. ጠቅላላ ጉባኤው በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡ ሆኖም እንደአስፈላጊነታቸው አስቸኳይ ስብሰባዎች ከማካሄድ አይታገድም;

3. The General Assembly shall hold its regular meetings once a month; notwithstanding, it shall not be prohibited to conduct urgent meetings, as deemed as, necessary;

4. ጠቅላላ ጉባኤው ከአባላቱ መካከል የሥራ አመራር ኮሚቴውን መርጦ ይሰይማል

4. The General Assembly shall nominate management committee from members of the council;

5. የቀበሌው ጠቅላላ ጉባኤ የክልሉን ስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ ስልጣንና ተግባር አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ /9/ ስር የሰፈሩትን ድንጋጌዎች እንደ አግባብነታቸው በስልጣን እርከኑ መሠረት ሊሠራባቸው ይችላል፡፡

5. The kebele General Assembly may be able to use those provisions stipulated, under Article /9/ of this proclamation as deemed as, necessary to its level of powers.

6. ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት መካከል 2/3ኛ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ሲገኙ ምልዐተ-ጉባኤ ይሆናል;

6. where 2/3 members, among the General Assembly, are found in the meeting, the quoum shall be held;

7. የጠቅላላ ጉባኤው ውሣኔ የሚተላለፈው በስበሰባው ላይ በተገኙ አባላት የአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡ ሆኖም ድምፁ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ስብሳቢው የደገፈው ሀሣብ የጉባኤው ውሣኔ ሆኖ ያልፋል፡፡

7. Decision of the General Assembly, shall be passed by a majority vote of its members; Notwithstanding , the decision that shall be supported by the chief Administrator , shall be the decision of Assembly in case of a tie.

25. ስለ ቀበሌ ሥራ አመራር ኮሚቴ

1. የሥራ አመራር ኮሚቴው ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት መካከል በምርጫ የሚሰየም አምስት አባላት ያሉት የቀበሌው ስነ-ሕዝብ ምክር ቤት አስፈፃሚ አካል ሲሆን ተጠሪነቱም ለቀበሌው የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ጠቅላላ-ጉባኤና ለቀበሌው ዋና አስተዳዳሪ ይሆናል፤

2. የቀበሌው የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የቀበሌውን የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ዕቅድ በማዘጋጀት ለቀበሌው ጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያስፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤

ለ/ በቀበሌው ከሚካሄደው የወሣኝ ኩነቶች ምዝገባ ለስታስቲክስ ሥራዎች የሚሆኑ መረጃዎችን በመለየት ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በየወቅቱ ይልካል፤

ሐ/ የቀበሌውን የስነ-ሕዝብ ጉዳይ መረጃዎች በየጊዜው በማደራጀት ለቀበሌው ልማት የሚያገለግሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤

መ/ በስነ-ሕዝብ መረጃ ላይ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ የቀበሌ አስተዳደር ወሰን ለውጦች ሲኖሩ በወቅቱ ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት ያሳውቃል፤

ሠ/ በስነ-ሕዝብ ጉዳዮች ላይ የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሣደግ ተከታታይነት ያለው የትምህርትና ቅስቀሣ ሥራዎችን ያከናውናል፣ ያስተባብራል፤

25. The Kebele Management Committee

1. The management committee of the Kebele , having been elected by the General Assembly of the Kebele population affairs council, shall have five members and serve as an executive body of the kebele council; and, it is accountable to the Assembly of the Kebele population affairs council; and, the pertinent Chief Administrator of the Kebele thereof.

2. the Kebele Management Committee shall have the following Powers and duties:

a) Prepare annual population work plan and executioner budget; and, have same to be approved by the General Assembly, upon the presentation and follow-up its execution.

b) Identify data, based on data generated from the Kebele Level vital registration system; and frequently send information for statistical manipulations to the Woreda Finance and Economy Development Office.

c) Create a conducive climate to frequently organize and generate data with regard to population issues pertinent to the development effort of the kebele.

d) Report to the Woreda Finance and Economic Development Office as to any Administrative Boundary Changes that affects the population and related data thereof.

e) Constantly keep the population of the kebele aware of population and related issues through coordinating and actively participating in educating the same.

ረ/ በቀበሌው ውስጥ በስነ ሕዝብ ጉዳይ ላይ የሚሠሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን እንቅስቃሴ ይከታተላል፣ ድጋፍ ይሠጣል፤

ሰ/ በቀበሌው ደረጃ የስነ-ህዝብ ጉዳዮችን አፈፃፀም አስመልክቶ የተጠቃለለ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቀበሌው አስተዳደር ጽ/ቤትና ለወረዳው ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት በየወቅቱ ያስተላልፋል፤

ሸ/ ከስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት እና ከወረዳ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ጽ/ቤት የሚሠጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባራት ያከናውናል፡፡

ክፍል አምስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26. ስለ ም/ቤቱ የገቢ ምንጭ

የም/ቤቱ የገቢ ምንጮች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

1. መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች፣ ከበጐ አድራጊ ግለሰቦችና ከአበዳሪ ተቋማት የሚገኝ የገንዘብና የቁሣቁስ ድጋፍ ወይም ብድር፤
2. በክልሉ መንግስት የሚመደብ በጀት፡፡

27. ስለ ም/ቤቱ የበጀት ዓመት

የም/ቤቱ የበጀት ዓመት የክልሉ መንግስት የሚሠራበት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

28. ስለ በጀት አስተዳደርና የሂሣብ አያያዝ

1. ም/ቤቱ በስሙ የራሱን ተንቀሣቃሽ የባንክ ሂሣብ ይከፍታል፤
2. የም/ቤቱ ሂሣብ በየበጀት ዓመቱ መጨረሻ በገለልተኛ ኦዲተሮች እንዲመረመር ይደረጋል፡፡

29. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

የስነ-ሕዝብ ጉዳዮችን አስመልክቶ እስከ አሁን ድረስ በክልሉ ፀንቶ የሚሠራበት ማናቸውም መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ ሆኖ ከተገኘ ይህንን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

f) Coordinate the activities of governmental and non governmental organizations working on population and related issues and create suitable conditions for integration of efforts as between and among them.

g) Prepare comprehensive periodic reports with regard to the activities undertaken on population affairs and send to woreda administrative office and woreda Finance and Economic Development office.

h) Carry out other reated functions, that shall be renderd by the population affairs council and the woreda finance and economic development office.

PART FIVE

MISCELLANEOUS PROVISIONS

26. Source of Income of the Council

The in come of the Council, shall be drawn from the following sources:

1. Financial and material support or credit obtained from governmental and non-governmental organizations, charitable individuals and credit rendering institutions.
2. The allocated Budget from the Regional Government.

27. Fiscal Year of the Council

The Fiscal Year of the Council shall be identical with the Fiscal Year, which the Regional State utilizes.

28. Budget Administration and Book Accounts

1. The council shall open its own current bank account.
2. The Account of the Council shall be audited by independent or impartial auditors at the end of each and every year.

29. Inapplicable Laws

Any directives or customary practices, that have been still in effect throughout the Region; Pursuant to population issues, shall not be applicable on matters, that are contrary to this proclamation therein.

30 አዋጁን ስለማሻሻል

ይህ አዋጅ እንዲሻሻል የክልሉ የስነ-ሕዝብ ጉዳይ ም/ቤት ጠቅላላ ጉባኤ 2/3ኛው ድምጽ የወሰነ እንደሆነ ጉዳዩ ለብሔራዊ ክልሉ ም/ቤት ቀርቦ ሊሻሻል ይችላል፡፡

31 የመተባበር ግዴታ

1. ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በዚህ አዋጅ አንቀጽ /4/ ለተጠቀሱት የም/ቤቱ አላማዎች ተፈፃሚነት የመተባበር ግዴታ አለበት፤

2. ማንኛውም የክልሉ መንግስታዊ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት ከመደበኛ ተግባርና ኃላፊነቶቹ ጐን ለጐን የስነ-ህዝብ ጉዳይ ሥራዎችን አጣምሮ እንዲያከናውን በዚህ አዋጅ ኃላፊነትና ግዴታ ተጥሎበታል፡፡

32. ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1. ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች የክልሉ መስተዳድር ም/ቤት ሊያወጣ ይችላል፤

2. የስራ አመራር ቦርዱ ይህንን አዋጅ እና በአዋጁ መሠረት የሚወጡትን ደንቦች ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

33. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግስት ዝክረ-ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባህር ዳር

ሐምሌ 04 ቀን 2005 ዓ.ም

አያሌው ጉበዜ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ፕሬዚዳንት

30. Amendment of the Proclamation

This proclamation may be amended upon presentation to the Council of the National Regional State; where two-thirds vote of the Council of the General Assembly of population Affairs decide to be amended thereof.

31. Duty to Cooperate

1. Any person whether natural or juridical, shall have a duty to cooperate for the applica bility of objectives, stipulated of this council; under Art. 5 of this proclamation.

2. Any Regional Government sector or Organization belonging shall have a responsibility and duty by this proclamation, to carry out activities of Population Affairs besides with its regular duties and responsibilities.

32. Power to Issue Regulations And Directives

1. The Council of the Regional Government may issue regulations necessary for the execution of this proclamation.
2. The Board of management may issue directives, necessary for the implementation of this proclamation and the regulations to be issued pursuant to this proclamation thereof.

33. Effective Date

This proclamation shall come into force, as of the date of publication in the Regional Zikre – Hig Gazzettee.

Done at Bahir Dar,

This 11th day of July, 2013.

Ayalew Gobezie

President of Amhara National Regional State